## የTCTዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

2015 ሰኔ | ቅጽ 1 | ቁጥር 14

**TCTዝብላክ ኢትዮጵያ በ3.5 ሚሊዮን ብር ተመን ለ 15 ቀናት የሚቆየውን ሁለተኛ ዙር የTSM ፕሮጀክት አክሲዮን ሽያጭ ማስጀመሩን አበሰረ።**

ምስል በ ነብዮ ዳንኤል



**"የTCTዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ግንቦት 01 ቀን 2015 ዓ.ም ለTCTዝብላክ ሠራተኞች እና ለጋዜጠኞች የኩባንያውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ እና Tower Shareholder Model(TSM) ፕሮጀክትን የተመለከተ ማብራሪያ በሰጡበት ጋዜጣዊ መግለጫ የሁለተኛውን ዙር አክሲዮን ሽያጭ መጀመር አብሥረው በማስታወቂያ ዋጋ ከግንቦት 21 እስከ ሰኔ 05 2015 ዓ.ም ለአንድ ሺህ ሰዎች ተዘጋጅቶ የነበረው የመጀመሪያ ዙር አክሲዮን ሽያጭ ለመርሐግብሩ የታቀዱት ባለአክሲዮኖች ቁጥር መሟላትን ተከትሎ ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ.ም መጠናቀቁንም አስታውቀዋል።**

ኩባንያችን የተሠማራባቸውን ፕሮጀክቶች በተመለከተ ያለውን ተጨባጭ እውነታ ለማስረዳት በተዘጋጀው ጋዜጣዊ መግለጫ የመንግሥትና የግል ሚዲያ ተቋማት፣ እንዲሁም የማኅበራዊ ትስስር ገጾች አዘጋጆች የተሳተፉ ሲሆን በተለያዩ ዙሮች እየተከናወነ የሚገኘውን የቲኤስኤም ፕሮጀክት አክሲዮን የማስታወቂያ ሽያጭ በተመለከተም በኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጠለቅ ያለ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ መስሕብነት ያለውን ባለ 115 ወለል የከገበሬው ታወር እና ሌሎች ለመኖሪያ፣ ለገበያ፣ ለመዝናኛ እና ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉ ሕንጻዎችን ለመገንባት ባሰናዳው ቲኤስኤም ፕሮጀክት ከሚገነቡት አፓርትመንቶች መካከል በማስታወቂያ ዋጋ በተዘጋጀው የ1.5 ሚሊዮን ብር አክሲዮን ሽያጭ ለተሳተፉ 1000 ባለአክሲዮኖች 100 ካሬ ሜትር ላይ የሚያርፈውን ባለ 3 መኝታ መኖሪያ ቤት በስጦታ የሚያገኙበትን ልዩ ዕድል ተጠቃሚ ማድረጉም በመግለጫው ተጠቅሷል።

ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ በመግለጫቸው ከሰኔ 01 እስከ ሰኔ 16 2015 ዓ.ም ድረስ ለ 750 ባለአክሲዮኖች ብቻ የተዘጋጀው የሁለተኛው ዙር የቲኤስኤም ፕሮጀክት የማስታወቂያ አክሲዮን ሽያጭ ዋጋ 3.5 ሚሊዮን ብር መሆኑን እና በቅድሚያ 3 ሚሊዮን ብር ተከፍሎ ቀሪው የ500 ሺ ብር ክፍያ በ5 ዓመት ውስጥ እንደሚፈጸም ገልጸው አክሲዮኑን በመግዛት የፐርፐዝብላክ ቤተሰብ ለሚሆኑት 750 ባለአክሲዮኖች ከታሪካዊው ከገበሬው ታወር አቅራቢያ ከሚገነባው እና B+G+65 ወለል የሚኖረው አፓርትመንት ላይ 100 ካሬ ሜትር ይዞታ የሚሸፍን ባለ 3 መኝታ መኖሪያ ቤት በስጦታ የሚያስገኝላቸው መሆኑን አስረድተዋል።

ፐርፐዝብላክ ኢቲኤች የጥቁር ሕዝብን ክብር በኢኮኖሚያዊ ልዕልና ለማረጋገጥ በግብርናው ዘርፍ ላይ ትኩረቱን በማድረግ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ የተናገሩ ሲሆን በአገራችንም ሆነ በመላው ጥቁር ማኅበረሰብ ዘንድ ለሚፈለገው ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ገበሬው ቁልፍ ድርሻ ያለው በመሆኑ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ በማፍሰስ የግብርናውን ዘርፍ የሚያዘምኑ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

ምስል በ ነብዮ ዳንኤል



**"በኩታ ገጠም አስተራረስ 10 ሺህ ክላስተሮችን በማደራጀት 1 ሚሊዮን ገበሬዎችን የTCTዝብላክ ባለአክሲዮን እና የዘመናዊ እርሻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ለማድረግ የታቀደበት የከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር አጠቃላይ በጀት 350 ቢሊዮን ብር መሆኑን ያወሱት ዋና ሥራ አስፈጻሚው የከገበሬው ታወር ሼር ሆልደር ሞዴል የኩባንያውን የገንዘብ አቅም ለማደርጀት ከሚያስችሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች አንዱ መሆኑንም አብራርተዋል።**

ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ የ Tower Shareholder Model (TSM) ፕሮጀክት ጅማሬ ለኩባንያው ሠራተኞችና ለሚዲያ ተቋማት ከ6 ወራት በፊት ይፋ መደረጉን አስታውሰው በቅርቡ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ሜክሲኮ አካባቢ ባገኘው ቦታ ላይ ከታሪካዊው ባለ 115 ወለል የከገበሬው ታወር በተጨማሪ ለመኖሪያ፣ ለመዝናኛ፣ ለገበያ፣ ለቢሮ እንዲሁም ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉ ሕንጻዎች ግንባታ ሒደት ለማከናወን ዝግጅት ላይ መሆኑን አስታውቀዋል።

የሰው ልጅ ለመኖር ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ፍላጎቶች መካከል ዋናዎቹ ምግብና መጠለያ በመላው አፍሪካ በበቂ ሁኔታ አለመሟላታቸውንና ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያም ምርትና ምርታማነትን በመጨመር የገበያ ዋጋን ለማረጋጋትና የኑሮ ውድነትን ታሪክ ለማድረግ በትኩረት ከመሥራት ባለፈ በብሔራዊ ደረጃ የምግብና ዋስትናን ለማረጋገጥ ልዩ ልዩ መርሐግብሮችን ነድፎ ሲንቀሳቀስ መቆየቱን የተናገሩት ዋና ሥራ አስፈጻሚው በአሁኑ ወቅት የመጠለያ ዋስትናን ለማረጋገጥ የከበሬውን ታወር ለመገንባት ቅድመ ዝግጅቶችን መጀመሩን ገልጸዋል።

Tower Shareholder Model (TSM) ፕሮጀክት የኩባንያውን ካፒታል በብዙ እጥፍ ከማሳደጉ ባሻገር የፐርፐዝብላክን የኢንቨስትመንት ፍላጎት በቀጥታ ከደንበኞች ፍላጎት ጋር በማገናኘት እጅግ በቅናሽ ዋጋ የአክሲዮን እና የቤት ባለቤት እንዲሆኑ የሚያስችላቸው መሆኑንና ለከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሐግብርም ቋሚ የገቢ ምንጭ በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው ዋና ሥራ አስፈጻሚው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ተናግረዋል።



**የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ በአነስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ 1000 ባለአክሲዮኖችን ተጠቃሚ ለማድረግ በመጀመሪያው ባለ 54 ወለል ሕንጻ ውስጥ 100 ካሬ ላይ የሚያርፍ ባለ 3 መኝታ ቤት በ 1.5 ሚሊዮን ብር የማስተዋወቂያ ቅናሽ ዋጋ ቀርቦ እና ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ ጊዜ አስቀድሞ በስኬት መጠናቀቁን በማንሣት ከሰኔ 1 ጀምሮ እስከ ሰኔ 16 በሚቆየው 2ኛ ዙር የአክሲዮን ሽያጭ መርሐግብር 750 መካከለኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበው የከገበሬው ታወር ግዙፍ ግንባታ ሲጠናቀቅም ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ከመሆን ባሻገር እንደአገር የላቀ ኩራት ምንጭ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ታሪካዊ ሕንፃ ግንባታ ላይ ሁሉም አሻራውን እንዲያሳርፍ እና ተጠቃሚ እንዲሆን የግብዣ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።**

በዕለቱም ለጋዜጠኞች እና ለፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ከተሰጠው ማብራሪያ በተጨማሪ የኩባንያው የግንባታና ምሕንድስና ሥራዎች አማካሪ አቶ ናኦሊ ዳዲ የ Tower Shareholder Model (TSM)ን ፕሮጀክት አፓርትመንቶችን አጠቃላይ ገጽታ በተመለከተ በምስል የተደገፈ ገለጻ ሰጥተዋል።

## ፐርፐዝብላክ ግሎባል በደቡብ ሱዳን እና ታንዛንያ ቅርንጫፎችን በመክፈት በመላው አፍሪካ ተደራሽነቱን ለማስፋት እንቅስቃሴ መጀመሩን አስታወቀ።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በደቡብ ሱዳን እና ታንዛንያ ተነሳሽነቱን ተደራሽ ለማድረግ ከአገራቱ ተወካዮች ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ መፈራረሙን የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አፍሪካ ሙቭመንት አስተባባሪ አቶ ኢዮብ ዳንኤል አስታውቀዋል።

ፐርፐዝብላክ ግሎባል በመላው ዓለም የሚገኘውን ጥቁር ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ አቅም በማዳበር የተከበረ ማኅበረሰብ ለመገንባት ወጥኖ በኢትዮጵያ በጀመረው እንቅስቃሴ በርካታ ገንቢ ውጤቶችን ማስመዝገቡ የሚታወቅ ሲሆን ይህንን መልካም ተሞክሮ ለሌሎች የአፍሪካ አገራትም በማካፈል ላይ መሆኑ ተገልጿል።

ባሳለፍነው ሳምንትም ከታንዛንያ ተወካይ ፍራንሲስ ዌይሰን ሙኒር እና ከደቡብ ሱዳኑ ዲንግ ላም  ዩል ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ የተፈራረመ ሲሆን እንደ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ሁሉ ፐርፐዝብላክ ደቡብ ሱዳን እና ፐርፐዝብላክ ታንዛንያ በሚል ስያሜ በተጠቀሱት አገራት በራሳቸው ዜጎች መሥራችነት ለማቋቋም ከስምምነት ላይ ደርሷል።

በስምምነት ሰነዶቹ ላይ በሰፈረው መሠረት የገበሬዎችን ኢኮኖሚያዊ አቅም መገንባት፣ ለሴቶችና ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠርና ሥራ አጥነትን መቀነስ፣ ብሎም ጥራት ያላቸውን የግብርና ውጤቶች በማምረት ገበያን ማረጋጋት እና ምርቶችን ለውጪ ገበያ በማቅረብ የውጪ ምንዛሪን ማስገኘት በዋናነት የሚተገበሩ ሲሆን ዘላቂነት ባላቸው እንቅስቃሴዎች ዜጎች ራሳቸውን ችለው ማየትን ራዕይ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ይሆናል።

ይህም ከሌሎች አገራት እርዳታና ጣልቃ ገብነት በጸዳ መልኩ የአፍሪካውያንን የራስ ኢኮኖሚያዊ አቅም ከማዳበር አኳያ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ይኖረዋል ተብሏል።

በሁሉም የአፍሪካ አገራት ተግባራዊ ለማድረግ የታቀደው የፐርፐዝብላክ ተነሣሽነት በውጪ አገራት የሚኖሩ ዜጎች በአገራቸው ልዩ ልዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ተሠማርተው ለሌሎች የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ከማስቻሉም በተጨማሪ  የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በመፍጠር ረገድ ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ያሉት አቶ ኢዮብ እኛ በአገራችን ኢትዮጵያ ያሉ የግብርና፣ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያና፣ ንግድ ዘርፎች ላይ ትኩረት አድርገን በመሥራት ውጤት ማስመዝገብ እንደቻልን እነሱም በአገራቸው ውጤታማ በሚያደርጓቸው እንደ ግብርናና የመሳሰሉት ዘርፎች ላይ በስፋት በመሠማራት ምርትና ምርታማነታቸውን መጨመር ይችላሉ ብለዋል።

**እንደ አቶ ኢዮብ ንግግር በኢትዮጵያ የታየው የፐርፐዝብላክ ተነሣሽነት ውጤታማነት በሌሎች የአህጉሪቱ ክፍሎችም የገበሬዎችን ሕይወት ለመለወጥ፣ በአህጉራዊ ቀጠናው የጨመረውን የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ለማቅለል ብሎም በኢኮኖሚ የዳበረ ማኅበረሰብን ለመፍጠር መነቃቃትን ፈጥሯል።**

**በቀጣይም በሁለቱም አገራት ከሚቋቋሙት የፐርፐዝብላክ አፍሪካ ቅርንጫፎች ጋር ልምድና መረጃዎችን የመለዋወጥ ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል የተባለ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘም ፐርፐዝብላክ ጋናን ለማቋቋም በርካታ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን አቶ ኢዮብ አክለው ገልጸዋል።**

Purpose
Black
AFRICA

በመጨረሻም ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የአፍሪካ አህጉር የኢኮኖሚ ዋልታ በሆነው ግብርና ላይ ትኩረቱን በማድረግ በከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር አማካኝነት በመላው አገሪቱ የሚገኙ አርሶ አደሮችን በክላስተሮች በማደራጀት የኩባንያው ባለአክሲዮን እያደረገ ሲሆን ለዘርፉ ሜካናይዜሽን ቋሚ የገቢ ምንጭ ለማስገኘትም በዚሁ የአገር መጋቢ ገበሬ ስም 115 ወለል ያለው ሰማይ ጠቀስ ሕንጻ ለመገንባት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መጀመራቸውን አስታውሰዋል።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በተሰማራባቸው ዘርፎች ሁሉ እንደ ከገበሬው ሕንጻ ያሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን ጽንሰ ሐሳብ ጨምሮ ልምድና ተሞክሮዎችን ለሌሎች አገራት በማጋራት የተነሣሽነቱን ግቦች ለመምታት አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋልም ተብሏል።

**በገበሬው ሕይወት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣትና የጥቁር ሕዝብን ኢኮኖሚያዊ ልዕልና ለማረጋገጥ በሚከናወነው የከገበሬው ታወር ግንባታ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በመሳተፍ አሻራውን እንዲያሳርፍ ጥሪ ቀረበ።**

የከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሐግብርን የገንዘብ አቅም በማጎልበት የግብርናውን ዘርፍ ሜካናይዜሽን እውን ለማድረግ ትልቅ አስተዋጽዖ ለሚኖረው የTSM ፕሮጀክት ትግበራ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እና ትውልደ ኢትዮጵያዊ እንዲረባረብ የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ቴክኒካል ኦፕሬሽን ዋና ኃላፊ አቶ አስናቀ ኃ/ሚካኤል ገለጹ።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ገበሬዎች እርሻቸውን ከኩባንያው ጋር በኩታ ገጠም የአስተራረስ ሥርዓት በማልማት ምርታማነታቸው እንዲጨምር ለማስቻል በተለያዩ ክልሎች 7 ማስተባበሪያ እንዲሁም 10 ቅርንጫፍ ቢሮዎችን መክፈት የቻለ ሲሆን በዘመናዊ እርሻ በዓመት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ማምረት እንዲችሉ እየተሠራ እንደሚገኝ ዋና ኃላፊው ተናግረዋል።

በመርሐግብሩ ከተደራጁ 5 ክላስተሮች መካከልም በአማራ ክልል ጃቢ ጠናን ወረዳ ዘር መዘራቱን የገለጹት ኃላፊው በተመሳሳይ በሲዳማ ክልል በተጀመረ ልማት 50 ሄክታር መሬት በበቆሎ መሸፈኑን አብራርተዋል። በተጨማሪም ይህ ውጤታማ ተሞክሮ በሌሎችም ክላስተሮች ተግባራዊ እንደሚደረግ በመግለጽ በኦሮሚያ ክልል አርሲ ስሬ የሚገኙ አርሶ አደሮች የምርጥ ዘር አቅርቦት እየተጠባበቁ እንደሚገኙም አስታውሰዋል።

የገበሬዎችን አስተራረስ በተመለከተ አሁን ላይ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ትራክተሮች፣ ቦይ ማውጫዎች እና ሌሎች ማሽነሪዎችን በውድ ዋጋ በኪራይ ለአርሶአደሮች እንደሚደርሱ ያነሡት ኃላፊው የከገበሬው ሕንጻ ግንባታ ሲጠናቀቅ ከገቢው 20 በመቶው በከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር አማካኝነት ለክላስተሮች ማስፋፊያ የሚውል በመሆኑ እነዚህንና መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ ዓይነተኛ መሣሪያ እንደሚሆን አስረድተዋል።

ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ሰዓት ድረስ 19,587 ገበሬዎች የፐርፐዝብላክን አክሲዮኖች በመሸጥ 6 ሚሊዮን 740 ሺህ 747 ብር መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን በ17ቱም ቅርንጫፎች ስለ ከገበሬው ሕንጻ ገለጻዎች ተደርገው ቁጥራቸው ጥቂት የማይባል ገበሬዎች ፍላጎት ማሳየታቸው ተጠቅሷል። ”የከገበሬው ሕንጻ እስከሚጠናቀቅ ምን ዓይነት የገንዘብ አማራጮች ለመርሐግብሩ ማስፋፊያ እንደአማራጭ ተቀምጠዋል ስንል ላቀረብንላቸው ጥያቄ ከ10 ያላነሱ ባንኮች በጋራ በመሰባሰብ ለኩባንያው የገንዘብ አቅም መፍጠር የሚችሉበትን አሠራር በመዘርጋት ላይ መሆናቸውን እና ከተለያዩ የቁጠባና ብድር ሰጪ ተቋማት ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በጥምረት መሥራት የሚቻልባቸውን አቅጣጫዎች በማስቀመጥ ላይ እገኛለን ነው ያሉት ኃላፊው።

በመጨረሻም በከገበሬው ሕንጻ እና የከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር መካከል ያለውን ቁልፍ ግንኙነት በመረዳት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ትኩረት መሥራት ይገባል ያሉት አቶ አስናቀ እንደአገር እልባት ሊሰጠው የሚገባውን የምግብ ዋስትና ጉዳይ እውን ለማድረግ ኩባንያው በተሰማራባቸው ዘርፎች ሁሉ የሚመለከታቸው አካላት በጋራ ሊቆሙ ይገባል ብለዋል።

ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ካለመታከት አርሶ በሚመግበው ትጉህ ገበሬ ሕይወት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ብሎም የጥቁር ሕዝብን ኢኮኖሚያዊ ልዕልና ለማረጋገጥ በሚደረገው የከገበሬው ታወር/ሕንጻ ግንባታ ላይ በመሳተፍ ታሪካዊ አሻራውን ሊያኖር ይገባል ሲሉ የአክብሮት ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

KIEP
KEGEBEREW INTEGRATED EXPANSION PROGRAM

KEGEBEREW
TOWER


**ዋና አዘጋጅ፡ ሰላማዊት ደበበ**
**ሲንየር ሪፖርተር፡ ጌታባለው ገ/ሐና**
**ሪፖርተር፡ ኤደን ደነቀ**


## ለበለጠ መረጃ


ስንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ

+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222

7151

www.purposeblackethiopia.com